የሰ/መ/ቁ. 31748

የካቲት 18 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

**አመልካች፡-** ይስማው ድረስ ቀረበ።

**ተጠሪ፡-** ይበልጣል ፍቅር ቀረበ።

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል።

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቤት ይለቀቅልኝ ጥያቄን መነሻ የደረገ ክርክር የሚመለከት ነው። ክርክሩ ሲጀመር ከሣሽ የነበረው የአሁኑ ተጠሪ ነው። በመልካች ላይ ክስ የመሠረተው ከአባቴና እናቴ በውርስ የተላለፈልኝን ቤት ከሕግ ውጪ ይዞብኛል እና ያስረክበኝ በማለት ነው። አመልካች ደግሞ ለክሱ በሰጠው መልስ ቤቱ በተጠሪ አባት በውል ገዝቶ በስሙም ግብር እየገበረ ከ19 ዓመት በላይ ይዞት እንደሚገኝ ገልጾአል። ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው በማለትም ተከራክሮአል። ክሱን የሰማው ፍ/ቤት የይርጋውንም ሆነ በፍሬ ነገር ረገድ የቀረበውን ክርክር ውድቅ በማድረግ አመልካች ቤቱን ለተጠሪ እንዲያስረክብ ወስኖአል። ጉዳዩን በይግባኝ የሰማው የምስራቅ ጎጃም ከፍተኛ ፍ/ቤትም በስር ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሣኔ አጽንቶአል።

እኛም አመልካች ሐምሌ 6 ቀን 1999 ዓ.ም. በፃፈው ማመልከቻ የቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል። አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው በአመልካች በኩል የቀረበው የይርጋ መቃወሚያ ውድቅ የተደረገበትን አግባብ ለመመርመር ነው። በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከሥር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል።



ግራ ቀኝ ወገኖች ከስር ጀምሮ ካደረጉት ክርክር እና የሥር ፍ/ቤቶች ከሰጡት ውሣኔ ይዘት መገንዘብ እንደቻልነው አመልካች አከራካሪውን ቤት ሊይዝ የቻለው ከተጠሪ አባት ጋር ባደረገው የቤት ሽያጭ ውል መነሻነት ነው። የሽያጭ ውሉ የተደረገው በ1980 ዓ.ም. ሲሆን፣ ይህን ውል መሠረት በማድረግም አመልካች ቤቱን በይዞታው ስር ከማድረጉም በላይ፣ ቤቱ ለሚገኝበት ከተማ ማዘጋጃ ቤት አቅርቦ በስሙም ግብር ሲከፍል እንደቆየ መዝገቡ ያስረዳል። ተጠሪ የቤት ይለቀቅልኝ ክስ የመሠረተው መጋቢት 3 ቀን 1999 ዓ.ም. ነው።

እንደምንመለከተው አመልካች ቤቱን የያዘው ከተጠሪ አባት ጋር ባደረገው የሽያጭ ውል መሠረት ነው። ገንዘቡንም በወቅቱ ለተጠሪ አባት የከፈለ ስለመሆኑ በክርክሩ ተመልክቶአል። ተጠሪ ቤቱ ከመሠረቱ የሱ አይደለም። የአባቱን ወራሽነት መሠረት አድርጎ ነው ክሱን የመሠረተው። ቀደም ሲል እንደተገለጸው አመልካች ቤቱን የያዘው ከ1980 ዓ.ም. ጀምሮ ሲሆን፣ ተጠሪው ክስ የመሠረተው ደግሞ በ1999 ዓ.ም. ማለትም ከ19 ዓመት በኂላ ነው። ከዚህ የተነሣም ወደክሱ ፍሬ ነገር ከመገባቱ በፊት አመልካች ያቀረበው የይርጋ መቃወሚያ አግባብነት ማየቱ ተገቢ ይሆናል። ተደጋግሞ እንደተገለጸው በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የውል ግንኙነት የለም።። የተጠሪ አባት በሕይወት በነበሩበት ጊዜ የውል ይፍረስልኝ ክስ መስርተው ክርክሩ ከመወሰኑ በፊት በመሞታቸው ምክንያት ተጠሪ ተተክቶ የክርክሩ ተካፋይ የሆነ ሳይሆን፣ የወራሽነት መብቱን መሠረት በማድረግ በራሱ ክስ አንደ መሠረተም ተገንዝበናል። በመሆኑም አመልካች ያነሳው የይርጋ መቃወሚያ መታየት ያለበት ከፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1677 እና 1845 አንፃር ነው። በፍ/ብ/ሕግ/ቁ.1677/1/ እንደተመለከተው ግዴታው ከውል የተገኘ ባይሆንም በፍትሐብሔር ሕጉ አራተኛ መጽሐፍ በአንቀጽ 12 ስር የተመለከቱት ስለ ውሎች በጠቅላላው የተቀመጡ ድንጋጌዎች ይፈጸሙባቸዋል። በእርግጥ የአንዳንድ ግዴታዎችን አመጣጥ ወይም አይነት በመመልከት በተቀጠሰው አንቀጽ ስር ከተመለከቱት ደንቦች የተለዩ ድንጋጌዎች በሕግ ተመልክቶ ከተገኘ

እነዚህ በተለይ የተመለከቱት ድንጋጌዎች አግባብነት እንደሚኖራቸው በተጠቀሰው ቁ. 1677/2/ ተመልክቶአል፡፡ ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪ የመሠረተውን ክስ በተመለከተ በተለይ አግባብ ያለው የይርጋ ደንብ የለም፡፡ ስለዚህም በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1845 የተደነገገው የአስር ዓመት ገደብ /ይርጋ/ ይፈጸምበታል፡፡ ክሱ የቀረበው ቤቱ በአመልካች ከተየዘ ከአሥራ ዘጠኝ ዓመት በኂላ በመሆኑም በዚሁ የይርጋ ደንብ ተቋርጧል ማለት ነው፡፡ እውነታው ይህ ከሆነ ደግሞ የሥር ፍ/ቤቶች በይርጋ ረገድ የቀረበውን የአመልካች መቃወሚያ ውድቅ ያደረጉት የለአግባብ ከሕጉ ውጪ ነው፡፡ ከዚህ የተነሣም አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. አቤቱታ የቀረበበት በሁለት እጅ እነሴ ወረዳ ፍ/ቤት ሚያዝያ 12 ቀን 1999 ዓ.ም. ተሰጥቶ የምስራቅ ጎጃም አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 18003 ሰኔ 12 ቀን 1999 ዓ.ም. በሰጠው ውሣኔ ያፀናው እንዲሁም የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 13294 ሐምሌ 3 ቀን 1999 ዓ.ም. በሰጠው ትዕዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. ተጠሪ በአመልካች ላይ የመሠረተው ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል በማለት ወስነናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



# የአሰሪና ሰራተኛ ህግ